## የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር__________/2009

## በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር_ ______/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

1. በዚህ ደንብ ውስጥ፦
   - ሀ/ "አዋጅ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፤
   - ለ/ "የተሻረው አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994(እንደተሻሻለ)፣የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 53/1985 ከነማያሻሻያዎቹ እና የነዳጅ አዋጅ ቁጥር 296/78 ከነማያሻሻያዎቹ ናቸው፡፡
2. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## <u>የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር</u>

### 3. <u>ሚስጥራዊ መረጃ ስለመስጠት</u>

የአዋጁ አንቀጽ 8(2) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ሰነድ ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ሰነድ ወይም መረጃ የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን በጽሑፍ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም እሱን ለሚወክለው ሰው ሲያቀርብ እና ዋና ዳይሬክተሩ ወይም እሱን የሚወክለው ሰው የተጠየቀው ሰነድ ወይም መረጃ እንዲሰጥ ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ምዝገባ

### 4. የማንነት የሰነድ ማስረጃ

1. ማንኛውም ግለሰብ ከሚያቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ከሚከተሉት አንዱን የማንነት የሰነድ ማስረጃዎች አብሮ ማቅረብ አለበት፤

   ሀ/ የአመልካቹን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር ፓስፖርት ገጽ የተረጋገጠ ቅጂ፣

   ለ/ የአመልካቹን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ የመንጃ ፈቃድ ገጽ የተረጋገጠ ቅጂ፣

   ሐ/ የአመልካቹን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ ገጽ የተረጋጠ ቅጂ፣

   መ/ የአመልካቹ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ወይም

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ባለስልጣኑ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሌላ ማንኛውም ማስረጃ እንዲያቀርብለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

3. በኩባንያ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኩባንያው የተቋቋመበትን ወይም የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

4. በሽርክና ማህበር የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከሽርክና ማህበሩ የምዝገባ ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

5. በሌላ ማንኛውም ድርጅት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከድርጅቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማንኛውም የመመስረቻ ወይም ማቋቋሚያ ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

### 5. የማንነት አካላዊ መረጃ

1. ለግለሰብ ምዝገባ ዓላማ ባለሥልጣኑ፡-

   ሀ/ የግለሰቡን ትክክለኛ ማንነት ለማረጋገጥ፣ወይም

   ለ/ የማንነት ስርቆትን ወይም ማጭበርበርን ለመከላከል፣

   አመልካቹን ግለሰብ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ከግለሰብ ጋር በተገናኘ "የማንነት አካላዊ መረጃ" ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ/ የፊት ገጽታ መለያ፣

ለ/ የጣት አሻራ መለያ፣

ሐ/ የድምጽ መለያ፣

መ/ የዓይን ክፍሎች(ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ፣

## ክፍል አራት
## የታክስ እንደራሴዎች

### 6. ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ

1. ለአዋጁ ዓላማ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 4(4) መሠረት በቋሚነት እንደሚሰራ ድርጅት በሚቆጠር 'ወኪል' ተብሎ በሚጠራ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውነው የንግድ ሥራ ወኪሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የታክስ እንደራሴ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደታክስ እንደራሴ የሚቆጠር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወኪል በአዋጁ አንቀጽ 2(40) መሠረት ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ ከሆነ ሌላ ማንኛውም ሰው ተጨማሪ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል አምስት
## የከባድ ችግር ሁኔታዎች

### 7. የታክስ ምህረት ገደብ

ሚኒስትሩ በአዋጁ አንቀጽ 51 መሠረት የሚሰጠው የታክስ እና የዘገየ ክፍያ ወለድ ምህረት የገንዘብ ጣሪያ 10,000,000( አስር ሚሊዮን) ብር ነው፡፡

## ክፍል ስድስት
## ቅጾችና ማስታወቂያዎች እና የታክስ ክፍያ

### 8. የሰነዶች አቀራረብ እና የታክስ አከፋፈል ሥርዓት

በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ታክስ ማስታወቂው ወይም ሌላ ሰነድ በሚከተለው አኳሃን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፡፡

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ 82(2) ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በማስተላለፍ ወይም በአንቀጹ መሠረት ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ክፍያ መፈጸም፣ ወይም

ለ/ በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በአካል በማቅረብ ወይም በፖስታ ለባለሥልጣኑ በመላክ.

## 9. የሰነዶች ማቅረቢያ እና የታክስ መክፈያ ቦታ

1. አንቀጽ 8(ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ ለሚያካሂድ ወይም ቅርንጫፍ ላለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ዋና የሥራ ቦታው በሚገኝበት ክልል ሰነዶችን ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፡፡
2. አንቀጽ 8(ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ ዋና ሥራውን የሚያካሂድበት ቦታ በሚገኝበት ክልል ሰነዶችን ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት።
3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ክልል” የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል።

## ክፍል ሰባት
## የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

### ምዕራፍ አንድ
### ኮሚሽኑ በስሚ ሂደት ያለው ሥልጣን

## 10. የኮሚሽኑ ሥልጣን

1. ኮሚሽኑ፣

ሀ/ ማስረጃ በቃለ መሃላ ወይም በማረጋገጫ መቀበል፣

ለ/ አንቀጽ 11(2) እንደተጠበቀ ሆኖ ስለስሚ ሂደቱ ማስታወቂያ በአግባቡ ደርሶት ያልቀረበ ወገን በሌለበት የስሚ ሂደቱን መቀጠል፣ ወይም

ሐ/ የስሚ ሂደቱን በቀጠሮ ማስተላለፍ፣

ይችላል፡፡

2. የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
3. በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት እንደምስክር ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ሰው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚጠራቸው ምስክሮች የሚከፈላቸውን ያህል የውሎ አበል የመከፈል መብት ያለው ሆኖ በኮሚሽኑ መመሪያ መሠረት ክፍያው ይፈጸማል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የኮሚሽኑ ውሳኔ

### 11. የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቋረጥ፣ስለመዝጋት ወይም እንደገና ስለማየት

1. ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለኮሚሽኑ ያቀረበውን ይግባኝ በማናቸውም ጊዜ ለኮሚሽኑ ሬጅስትራር የጽሑፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ማቋረጥ ወይም መተው የሚችል ሲሆን፣ ኮሚሽኑም ይህ በሚሆንበት ጊዜ ይግባኙን ይዘጋል፡፡

2. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት በአካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሳይቀረብ የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡

3. የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ ፊት ቀርቦ በተደጋጋሚ ይግባኙን ያልተከታተለ እንደሆነ ወይም ከይግባኙ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የሚሰጠው ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ፕሬዝዳንቱ ስለኮሚሽኑ ሆኖ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡

4. ኮሚሽኑ በንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት ይግባኝ የዘጋ እንደሆነ፣ይግባኝ ባዩ የይግባኙ መዘጋት ማስታወቂያ በደረሰው በ30(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኙ እንደገና እንዲታይለት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል፡፡

5. በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፣ በፕሬዚደንቱ የሚሰጥ ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ይግባኙን እንደገና ሊያይ ይችላል፡፡

### 12. በተከራካሪ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ስምምነት

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው በይግባኙ ስሚ ማንኛውም ደረጃ ከይግባኙ ወይም ከይግባኙ ከፊል ጉዳይ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ ስለሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ ሲስማሙ ነው፡፡
2. ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ ከሆነ እና ስምምነት የተደረሰው ኮሚሽኑ ከሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ እንደሆነ፣ ኮሚሽኑ በሁኔታዎቹ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ ከሆነ እና ስምምነት የተደረሰው በይግባኙ ከፊል ጉዳዮች ላይ እንደሆነ፣ ኮሚሽኑ በይግባኙ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የስምምነቱን ሁኔታዎች ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 13. ለባለስልጣኑ ስለሚመለስ ውሳኔ

1. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 91 መሠረት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ/ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ እንደገና እንዲመለከተው ለባለሥልጣኑ ሲመልስ፣ ባለሥልጣኑ ኮሚሽኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ከግምት በማስገባት፣

   ሀ/ ይግባኝ የሚቀርብበትን ውሳኔ ማጽናት፣

   ለ/ ይግባኝ የሚቀርብበትን ውሳኔ ማሻሻል፣ ወይም

   ሐ/ የአዋጁ አንቀጽ 91(6) ተፈጻሚ ሲሆን የታክስ ስሌቱን ከፍ ማድረግን ጨምሮ ይግባኝ የሚባልበትን ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት፣

   ይችላል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ የሚቀርብበትን ውሳኔ ሲያሻሽል ወይም ሲተው፣የተሻሻለው ወይም የተሰጠው አዲስ ውሳኔ በኮሚሽኑ በይግባኝ እየታየ እንዳለ ይግባኝ የሚቀርብበት ውሳኔ የሚቆጠር ሲሆን፣ይግባኝ ባዩ ባቀረበው ይግባኝ ሊቀጥል ወይም ይግባኙን ሊያነሳ ይችላል፡፡

## 14. ውሳኔ ስለማረም

1. ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሠረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሻሻለው ይዘት በኮሚሽኑ እንደተሰጠ ውሳኔ ይቆጠራል፡፡
3. የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፣

   ሀ/ የህትመት ወይም የአጻጻፍ ስህተትን፣ ወይም

ለ/ በውሳኔ እና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይ ማንኛውንም አለመጣጣም፣

ይጨምራል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የኮሚሽኑ አስተዳደር

15. **ስሚ የሚካሄድበት ቦታ**

የኮሚሽኑ የክርክር ስሚዎች የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት በሚወስነው ቦታ ይካሄዳሉ፡፡

16. **ወጪዎች**

ወጪን በሚመለከት ኮሚሽኑ ተገቢ እና ምክንያታዊ መስሎ የሚታየውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

17. **ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ስለማቅረብ**

ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚገባ ማንኛውም ሰነድ በኮሚሽኑ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት፡፡

18. **ሰነዶች የሚሰጡበት አድራሻ**

ይግባኝ ባይ ከይግባኙ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ማንኛውም ሰነድ አድራሻውን በጽሑፍ ማስታወቂያ ለሬጅስትራሩ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት
## ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

19. **የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ስለመሆን**

1. ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆነ ሰው ይቆጠራል፡፡

   ሀ/ በታክስ፣በሂሣብ አያያዝ፣ በንግድ ሥራ፣በሕግ፣በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ከዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ የትምህርት ማስረጃ ያለው እንደሆነ፣ እና

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት፣

(1) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት፣ ወይም

(2) እንደታክስ ሠራተኛ በማገልገል፣

የሁለት ዓመት የሙሉ ጊዜ የሥራ ልምድ ያለው እንደሆነ፡፡

2. አንድ ግለሰብ በንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) ከተመለከተው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ልምድ በሌላ ሀገር ያገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ግለሰቡ የንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) መስፈርትን እንዳሟላ አድርጎ ሊወስደው ይችላል፡፡

3. የሚከተሉት ግለሰቦች የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው አይቆጠሩም፡፡

ሀ/ ዕዳውን መክፈል ያልቻለ የከሰረ ግለሰብ፣

ለ/ በስነምግባር ጉድለት በሙያ ማህበር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ፣

ሐ/ ከእምነት ማጉደል ጋር በተገናኘ ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ግለሰብ፣

መ/ በተሻረው አዋጅ ጭምር የታክስ ግዴታውን ያለመወጣት ሪከርድ ያለበት ግለሰብ፣

## ክፍል ዘጠኝ
## መሸጋገሪያ

### 20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በተሻረው አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው "የቀድሞ ኮሚሽን" ተብሎ ለሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የተሾሙ አባላት አገልግሎት በአዋጁ መሠረት "አዲሱ ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር ይቋረጣል፡፡

2. ንዑስ አንቀጽ (1) የሚመለከተው ሰው በአዋጁ አንቀጽ 87 መሠረት ለአዲሱ ኮሚሽን አባልነት ለመታጨት ብቁ ይሆናል፡፡

3. በአዋጁ አንቀጽ 87(3)(ለ) "የታክስ ሕግ" በሚል የተጠቀሰው የተሻረውን አዋጅ ይጨምራል፡፡

4. ለቀድሞው ኮሚሽን የቀረበ ይግባኝ ኮሚሽኑ ሥራውን ከማቆሙ በፊት ውሳኔ ያላገኘ እንደሆነ፣ የአዲሱ ኮሚሽን ፕሬዚደንት የሚሰጠው ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኙ በአዲሱ ኮሚሽን ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## <u>ክፍል አስር</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 21. <u>*መመሪያዎች*</u>

ሚኒስትሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 22. <u>ደንቡ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ…………..ቀን 2009 ዓ.ም

ኃይለማሪያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር